

## በኢትዮጵያ የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ፣

## ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ እና ምክር አገልግሎት ምርምር ዘርፍ

# ከኦገስት 11-20/2025 የነበረዉ የአየር ሁኔታ

# ግምግማ እንዲሁም

# ከኦገስት 21-31 እና ከሴፕቴምበር 1-10/2025

# የሚኖረው የአየር ሁኔታ ትንበያ እና ምክረ ሃሳብ

ኦገስት 2025

አዲስ አበባ

ስልክ+2511155383394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et


# በኢትዮጵያ የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ፣ ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ እና ምክር አገልግሎት ምርምር ዘርፍ

## 1. እ.ኤ.አ ከኦገስት 11 እስከ 20/2025 የነበረው የአየር ሁኔታ

ባለፉት አስር ቀናት በአብዛኛዉ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ የተሻለ የደመና ሽፋን እና ክምችት ነበራቸው፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ በምዕራብ፣ ሰሜን ምዕራብ፣ ሰሜን፣ መካከለኛዉ እና ምስራቅ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን ያለዉ ዝናብ ተመዝግቧል፡፡ በተጨማሪም በ24 ሰዓት ዉስጥ ከ30 ሚ.ሜ በላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ተመዝግቧል፡፡ ለአብነትም በአዲስ አበባ ቦሌ 39፣ ሀዋሳ 37፣ ባህር ዳር 44.3፣ 68.4፣ 36.8፣ ኮምቦልቻ 69.9፣ ደብረ ማርቆስ 39.7፣ ድሬ ደዋ 32.8፣ መተሃራ 46፣ ነቀምት 47.7፣ 30.7፣ 47፣ 39.3፣ 37፣ አቦምሳ 46፣ አዲስ አበባ ጥቁር አንበሳ 35.3፣ አደዋ 46.2፣ አዲግራት 60፣ አይደር 33፣ አይራ 31.2፣ 30.2፣ 46.8፣ ሀሮማያ 42.2፣ አልጌ 50፣ አማን 47.6፣ 41.8፣ አምደወርቅ 36.8፣ 39.3፣ አርጆ 32.4፣ 34.2፣ 36.8፣ አሶሳ 38፣ አጽቢ 33.6፣ 47.5፣ 48፣ አክሱም 30፣ ባቲ 59.5፣ ቡሂ 30.5፣ ቡለን 30.4፣ 40.4፣ ቡረጂ 31፣ ቻግኒ 42.6፣ ጨፋ 37.4፣ ጭፍራ 46.4፣ 70፣ ጭራ 36.2፣ 45፣ ዳንግላ 50.5፣ ደባርቅ 80.6፣ ደብረ ብርሃን 32.2፣ ደብረ ታቦር 37.9፣ 31.7፣ 33.6፣ ደብረ ወርቅ 48.4፣ እነዋሪ 59.2፣ 37፣ ፍቼ 32.2፣ ፉኙዶ 37፣ 56.6፣ ጋምቤላ 34.8፣ ጋቲራ 34.5፣ 31.2፣ ገልምሶ 34.5፣ 43.4፣ 48.5፣ ገዋኔ 32.4፣ ወሊሶ 44.6፣ ጊዳ አያና 32፣ ጊምቢ 43.5፣ 38.1፣ ጉንዶ መስቀል 32.2፣ ጅንካ 31.6፣ 36.4፣ ላሊበላ 36፣ 46.9፣ ላሬ 48.7፣ 36፣ ሊሙገነት 31.5፣ ማይጨዉ 43.2፣ ማንኩሽ 32.4፣ 33.4፣ ማሻ 30.2፣ መሃል ሜዳ 43.1፣ መኢሶ 31.2፣ 52.1፣ መካነ ሰላም 34.5፣ 34.7፣ መተማ 53.7፣ ሞጣ 81፣ አዳማ 52.1፣ 88.3፣ ነጆ 64.1፣ ኑራ ኤራ 33.8፣ 79.4፣ ሰንቃጣ 46.1፣ 68.9፣ ሻዉራ 56.6፣ ሽሬ 70.5፣ 36፣ 49.3፣ ሾላ ገበያ 57.1፣ ሲሪንቃ 40.8፣ 35፣ ቴፒ 31.2፣ ተረጫ 35.6፣ ጽጺቃ 52.6፣ ወገል ጤና 36፣ 32፣ አዲሰ ዘመን 42.3፣ 35.2፣ 32፣ 45.1፣ አቃቂ 36.3፣ አሺ 32.4፣ አሸሪ 65.7፣ አታንጎ 33፣ 45.5፣ ቢላምቢሎ 33.5፣ 31.4፣ ቦቁሳ 48.5፣ ቦርቃ 40፣ 43.1፣ 49.2፣ ቡልቂ 30.5፣ ጨለንቆ 57.6፣ መንደር ሰባት 10.7፣ ደበረ ሲና 30.7፣ 68፣ ደጋን 74.8፣ ደንግጎ 31.4፣ ደራ 30፣ 30.5፣ እነዳባጉና 31.3፣ ፈረስ ቤት 41፣ ጋሽና 80.9፣ 32.9፣ ጊናገር 40.7፣ 32.8፣ ጉበይሬ 37.9፣ 56.3፣ 60.3፣ 42.2፣ 39.6፣ 54.5፣ 39.5፣ ጉጉፍቱ 64.2፣ ሀገረ ሰላም 34.7፣ ሃርቡ 32.3፣ ሃሮ 50.2፣ 60.2፣ 50.2፣ 30.2፣ 40.8፣ ሂርና 42.5፣ 30.2፣ ካራሚሌ 42.8፣ 50.6፣ ቀርሳ 34.2፣ ቅዳሜ ገበያ 57.6፣ 37.6፣ 36.9፣ 58.8፣ 47.9፣ ኮበን 33፣ 31፣ 37.5፣ ቂልምስቅ 37.3፣ 31.1፣ ቁሉቢ 60.5፣ ኩሚ 53.5፣ 31.6፣ ማርዬ 45.6፣ 62.5፣ 43.3፣ ማያንሳ 43.2፣ መንዲዳ 44.3፣ መርሳ 35.4፣ 42.6፣ 55.6፣ መርጦለማርያም 37.5፣ ሞላሊ 34.3፣ ሙጊ 45.7፣ ሙጃ 36.8፣ ኖፓ 43.5፣


ሮብ ገበያ 32.8፣ ሮቢት 48፣ 49.2፣ 35፣ 53.2፣ ሰዲቃ 35.6፣ ሰቆታ 32.5፣ ተርኮዲ 34.7፣ 32.5፣ ትንሹ መጢ 56.1፣ 40.7፣ ጽገሬዳ 41.1፣ ወግዲ 36.3፣ ዉቅሮ 56፣ 30፣ 34፣ 36፣ ያንፋ 35.2፣ 40.1፣ 33.2፣ 40.3፣ ያዮ 30.6፣ 45.8፣ ዬጪላ 35፣ መንደር 11 40፣ 32.5፣ የሪ 35፣ 65፣ 45፣ 45፣ ሃራ 34፣ 48፣ 30.3፣ 56፣ ዉቅሮ ማሪያ 35.2፣ 39.4፣ ኢዳግ አርቢ 32.5፣ 35.2፣ 47.5፣ 42.6፣ 40.8፣ አንኮበር 30፣ 40፣ 33.1፣ 47፣ 36.2፣ መቀሌ ኦብዞርባቶሪ 33፣ እንዲሁም ጎበዬ 37.9፣ 56.3፣ 60.3፣ 42.2፣ 39.6፣ 54.5፣ 39.5 ሚ.ሜ የሚደርስ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ተመዝግቦባቸዋል።

በአጠቃላይ ባለፉት አስር ቀናት በ132 የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ በ24 ሠዓት ዉስጥ ከ30 ሚ.ሜ በላይ የሆነ ከባድ መጠን ያለዉ የዝናብ መጠን ነበራቸዉ (ምስል 1)፡፡ በተጨማሪም በአንዳንድ የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ በሆኑ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ በ24 ሰዓት ዉስጥ 60.0-88.3 ሚ.ሜ የሚደርስ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ተመዝግቧል፡፡ ከ70 ሚ.ሜ በላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ከተመዘገበባቸው የሀገሪቱ አከባቢዎች መካከል አዳማ፣ ሞጣ፣ ጋሸና፣ ደባርቅ፣ ኑራ ኤራ፣ ደጋን፣ ሽሬ፣ ጭፍራ፣ ሃይቅ ይገኙበታል (ምስል 1)፡፡





ምስል፡1 ከኦገስት 11-20 በ24 ሰዓት ውስጥ ከ60 ሚ.ሜ በላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ የተመዘገበባቸው

ባለፉት አስር ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከሀገሪቱ ቦታ ሽፋን አንፃር ሲገመገም፤ ከኦሮሚያ ክልል የቄለም ወለጋ፣ ምዕራብ ወለጋ፣ ምስራቅ ወለጋ፣ ሆሮ ጉድሩ ወለጋ፣ ኢሉባቦር፣ ቡኖ በደሌ፣ ጅማ፣ ምዕራብ እና ምስራቅ ሀረርጌ፣ ሁሉም የሸዋ ዞኖች፤ ከአማራ ክልል የሰሜን፣ መካከለኛዉ፣ ምዕራብና ደቡብ ጎንደር ዞኖች፣ ሰሜን፣ ምስራቅና ምዕራብ ጎጃም፣ የባህርዳር ዙሪያ፣ የአዊ፣ ዋግ ህምራ፣ የሰሜን እና ደቡብ ወሎ እና የሰሜን ሸዋ ዞኖች፣ ከቤንሻንጉል ጉምዝ ካማሺ፣ መተከል፣ ማኦ ኮሞ፣ አሶሳ፣ ዞኖች፣ ከጋምቤላ ክልል አኝዋክ፣ መዥንግ፣ የኑዌር እና የኢታንግ ልዩ ወረዳ፤ ከትግራይ ክልል የምዕራብ፣ የሰሜን ምዕራብ፣ ምስራቅ፣ መካከለኛዉ፣ ደቡብ ምስራቅ እና ደቡብ ትግራይ ዞኖች፣ ከአፋር ክልል የቅልበቲ፣ ሃሪ፣ ጋቢ፣ ፋንቲ፣ አዉሲ እና ማሂ  ዞኖች፣ አዲስ አበባ፣ ድሬዳዋ እና ሐረሪ፣ ከሱማሌ ክልል የሲቲ እና ኤረር ዞኖች፣ ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ኮንታ፣ ዳዉሮ፣ ከፋ፣ ሸካ፣ ቤንች ሸኮ ዞኖች ላይ ከ61-580 ሚ.ሜ የሚደርስ ዝናብ ከ5-10 ቀናት ያህል ዝናብ ነበራቸዉ (ካርታ 1 እና 2)፡፡ በተጨማሪም የምዕራብ አርሲ፣ አርሲ፣ ምስራቅ ባሌ፣ ባሌ ዞኖች፤ ሁሉም የሲዳማ ክልል ዞኖች፣ ከማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ጉራጌ፣ ምስራቅ ጉራጌ፣ የሀዲያ፣ ስልጤ፣ የከንባታ፣ የሃላባ፣ የም ዞኖች፣ ቀቤና፣ ማረቆ፣ ጠምባሮ ልዩ ወረዳ፣ ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል የጎፋ፣ ወላይታ፣ ባስኬቶ፣ አሪ፣ ኮንሶ፣ ቡርጂ፣ አሌ፣ ጋርዱላ፣ ኮሬ እና ደቡብ ኦሞ ዞኖች ዞኖች፣ ከሱማሌ ክልል የፋፈን፣ ጃረር፣ ነጎብ፣ አፍዴር፣ እና የሊበን ዞኖች፣ ላይ ከ11-60 ሚ.ሜ የሚደርስ ዝናብ ከ2-6 ቀናት ያህል ዝናብ ነበራቸዉ (ካርታ 1 እና 2) ፡፡





ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከኦገስት 11 እስከ 20/2025 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ




ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከኦገስት 11 እስከ 20/2025 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸዉ ቀናት


ባለፉት አስር ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር ሲነፃፀር ከኦሮሚያ ክልል የቄለም ወለጋ፣ ምዕራብ ወለጋ፣ ምስራቅ ወለጋ፣ ሆሮ ጉድሩ ወለጋ፣ ኢሉባቦር፣ ቡኖ በደሌ፣ የምዕራብ አርሲ፣ አርሲ፣ ምስራቅ ባሌ፣ ባሌ ዞኖች፤ ጅማ፣ ምዕራብ እና ምስራቅ ሓረርጌ፣ ሁሉም የሸዋ ዞኖች፤ ከአማራ ክልል የሰሜን፣ መካከለኛዉ፣ ምዕራብና ደቡብ ጎንደር ዞኖች፣ ሰሜን፣ ምስራቅና ምዕራብ ጎጃም፣ የባህርዳር ዙሪያ፣ የአዊ፣ ዋግ ህምራ፣ የሰሜን እና ደቡብ ወሎ እና የሰሜን ሸዋ ዞኖች፣ ከቤንሻንጉል ጉምዝ ካማሺ፣ መተከል፣ ማኦ ኮሞ፣ አሶሳ፣ ዞኖች፣ ከጋምቤላ ክልል አኝዋክ፣ መዥንግ፣ የኑዌር እና የኢታንግ ልዩ ወረዳ፤ ከትግራይ ክልል የምዕራብ፣ የሰሜን ምዕራብ፣ ምስራቅ፣ መካከለኛዉ፣ ደቡብ ምስራቅ እና ደቡብ ትግራይ ዞኖች፣ ከአፋር ክልል የቅልበቲ፣ ሃሪ፣ ጋቢ፣ ፋንቲ፣ አዉሲ እና ማሂ  ዞኖች፣ አዲስ አበባ፣ ድሬዳዋ እና ሐረሪ፣ ከማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ጉራጌ፣ ምስራቅ ጉራጌ፣ የሀዲያ፣ ስልጤ፣ የከንባታ፣ የሃላባ፣ የም ዞኖች፣ ቀቤና፣ ማረቆ፣ ጠምባሮ ልዩ ወረዳ፣ ሁሉም የሲዳማ ክልል ዞኖች፣ ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል የጎፋ፣ ወላይታ፣ ባስኬቶ፣ አሪ፣ ኮንሶ፣ ቡርጂ፣ አሌ፣ ጋርዱላ፣ ኮሬ እና ደቡብ ኦሞ ዞኖች፣ ከሱማሌ ክልል የሲቲ፣ ኤረር፣ ፋፈን፣ ጃረር፣ ነጎብ፣ አፍዴር፣ የሊበን እና ዳዋ ዞኖች፣ ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል የከፋ፣ ኮንታ፣ ዳውሮ፣ ቤንች ሸኮ፣ ሸካ እና ምዕራብ ኦሞ ዞኖች ላይ  በአብዛኛዉ ከመደበኛው በላይ የሆነ የዝናብ መጠን ተመዝግቧል (ካርታ 3) ፡፡




ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከኦገስት 11 እስከ 20/2025 የነበረዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር ሲነፃፀር

## 1.2 እ.ኤ.አ ከኦገስት 11 እስከ 20/2025 የነበረው የአየር ሁኔታ በግብርና ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ


ባለፉት አስር ቀናት በአብዛኛው የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ በሆኑት የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ በመጠን ሆነ በስርጭት የተስፋፋና ብዙ ቦታዎችን ያዳረሰ የእርጥበት ሁኔታ ነበራቸው፡፡ ይህም ሁኔታ ቀደም ሲል በሚያዝያና ግንቦት ተዘርተው በመካከለኛና ፍሬ በመሙላት ላይ ለሚገኙት የረጅም ጊዜ ሰብሎች እንደ ማሽላና በቆሎ ለመሳሰሉት እንዲሁም በቅርብ ጊዜ ተዘርተው በተለያየ የዕድገት ደረጃ ላይ ላሉት እንደ ስንዴ፣ ገብስ፣ አጃ እና ጤፍ ለመሳሰሉት የብርዕ ሰብሎች፣ የጥራጥሬና የቅባት እህሎች፣ ለቋሚ ተክሎች የዉሃ ፍላጎት መሟላት ምቹ ሁኔታን ከመፍጠሩም በላይ በምስራቅና በሰሜን ምስራቅ ለሚገኙት አርብቶ አደሮችና ከፊል አርብቶ አደሮች የመጠጥ ውሃ እና የግጦሽ ሳር አቅርቦትን ከማሻሻል አንጻር አዎንታዊ ሚና ነበረው፡፡በአንፃሩ በአንዳንድ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ከነበረው ከባድና ተከታታይነት ካለው ዝናብ ጋር ተያይዞ የጎርፍ፣ የመሬት መንሸራተትና መሰንጠቅ እንዲሁም በሰብሎች ላይ የውሃ መተኛትና መጥለቅለቅ ሁኔታዎች ተከስተዋል፡፡ በተለይም አፋር ክልል ገዋኔ ወረዳ የጣለው ከባድ ዝናብ በእንስሳት ላይ ጉዳት አድርሷል፤ እንድሁም በዋግህምራ ብሔረሰብ አስተዳደር ጋዝጊብላ ወረዳ በረዶ ቀላቅሎ የጣለው ከባድ ዝናብ በተዘሩ ሰብሎች ላይ ጉዳት አድርሷል፡፡በተጨማሪም በሽሬ ከተማ እና ቢሾፍቱ ከተማ የጣለው ከባድ ዝናብ በንብረት ላይ ጉዳት አድርሷል (ካርታ 4) ፡፡




ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከኦገስት 11 እስከ 20/2025 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ

### 1.3 እ.ኤ.አ ከኦገስት 11 እስከ 20/2025 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባለፉት ቀናት በአብዛኛው አባይ፣ ኦሞ ጊቤ፣ ተከዜ፣ ባሮ አኮቦ፣ መረብ ጋሽ፣ አፋር ደናክል፣ አዋሽ፣ ስምጥ ሸለቆ፣ አይሻ፣ በላይኛው ዋቢ ሸበሌ፣ ገናሌ ዳዋ እና ኦጋዴን ተፋሰሶች ላይ ከመጠነኛ እስከ ከፍተኛ የሆነ የገጸ ምድር የውሀ ፍሰት ነበራቸው፡፡ በተጨማሪም በመካከለኛው አባይ እና በመካከለኛው ኦሞ ጊቤ፣ በላይኛው ተከዜ፣ አዋሽ እና ባሮ አኮቦ እጅግ በጣም ከፍተኛ የሆነ የገጸ ምድር የውሃ ፍሰት ነበራቸው (ካርታ 5)፡፡ ይህ ሁኔታ ለገፀ ምድር ውሃ ሀብት አዎንታዊ አስተዋፅዖ እንደ ነበረው የተተነተኑ የውሃ ሚቲዎሮሎጂ መረጃዎች ያመላክታሉ፡፡ ከዚህም ጋር ተያይዞ የመስኖም ሆነ የሀይል ማመንጫ ግድቦች የተሻለ የውሀ አቅም እንዲኖራቸው አድርጓል። ሆኖም እንደተከዜ እና ቆቃ በመሳሰሉ ግድቦች የገባው ከፍተኛ የውሀ መጠን በተለይም ለታችኛው የተፋሰሱ አካባቢዎች አስጊ ደረጃ ላይ የደረሰ እንደሆነ ታይቷል (ካርታ 5) ።




ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከኦገስት 11 እስከ 20/2025 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ


## 2. መግቢያ

በመደበኛ ሁኔታ የክረምት ዝናብ ቀደም ብሎ በደቡብ ምዕራብ እና በምዕራብ አጋማሽ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የሚጀምር ሲሆን፣ በሂደትም እየተጠናከሩ ከሚሄዱ ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ጋር ተያይዞ በኦገስት ወር ውስጥ የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ አካባቢዎች ሙሉ በሙሉ ዝናብ ያገኛሉ፡፡ የኦገስት ወር ከተቀሩት የክረምት ወራት በተሻለ ሁኔታ ሁሉንም የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ አካባቢዎችን በመጠንም ሆነ በሥርጭት ከፍተኛ ደረጃ የሚደርስበት ወር ነው። ስለሆነም የወሩ አማካይ የዝናብ መጠን በምዕራብ አጋማሽ በአብዛኛው የሀገሪቱ ሥፍራዎች ላይ ከ200-400 ሚ.ሜ እና በአንዳንድ ሥፍራዎች ላይ ከ400 ሚ.ሜ በላይ ይደርሳል። በእነዚህ አካባቢዎች የዝናብ ቀናትም በዚያው መልክ የሚጨምር በመሆኑ ከ18-30 ለሚደርሱት ቀናት ዝናብ ይኖራል። በሌላ በኩል በምስራቅ፣ በሰሜን ምስራቅ እና በመካከለኛው ኢትዮጵያ አካባቢዎች ላይም ቢሆን የዝናቡ መጠንና ሥርጭት እየተስፋፋ የሚሄድ በመሆኑ ከ6-20 ቀናት ያህል እስከ 300 ሚ.ሜ የሚደርስ ዝናብ በአማካይ ይኖራል።

በመደበኛ ሁኔታ በኦገስት የመጨረሻው አሥራ አንድ ቀናት ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች በበለጠ ሁኔታ እየተጠናከሩ የሚሄዱበት ጊዜ ነው፡፡ በተጨማሪም አልፎ አልፎ ባሉት ቀናት በፀሀይ ሃይል ታግዘው ከሚጠናከሩት የደመና ክምችቶች በአንዳንድ ቦታዎች ላይ በረዶ የቀላቀለ ከባድ መጠን ያለዉ ዝናብ ለወንዞች ሙላትና ለቅጽበታዊ ጎርፍ መከሰት አስተዋጽኦ ያደርጋሉ፡፡

### 2.1 እ.ኤ.አ ከኦገስት 21 እስከ 31/2025 የሚኖረው የአየር ሁኔታ ትንበያ


በኦገስት የመጨረሻው አሥራ አንድ ቀናት ለክረምት ዝናብ መፈጠር ምቹ ሁኔታን የሚፈጥሩ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ይበልጥ እየተስፋፉና እየተጠናከሩ ይሄዳሉ፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘም በምዕራብ፣ ሰሜን ምዕራብ፣ ሰሜን፣ ደቡብ ምዕራብ፣ መካከለኛው፣ ምስራቅ እና ሰሜን ምስራቅ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የተሻለ የዝናብ መጠንና ሥርጭት ይኖራቸዋል (ካርታ 6)። ስለሆነም እርጥበታማው የአየር ሁኔታ በተለይም በምዕራብ፣ ሰሜን ምዕራብ፣ ሰሜን ምስራቅ፣ ምስራቅ እና መካከለኛዉ የሀገራችን አከባቢዎች ላይ በመጠንም ሆነ በሥርጭት እየተስፋፋ ከመሄዱ ጋር ተያይዞ በብዙ ቦታዎቻቸው ላይ ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ይኖራቸዋል፡፡ በተጨማሪም በደቡብ ምዕራብ እና በደቡብ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚኖራቸዉ አሃዛዊ የትንበያ መረጃዎች ያመላክታሉ (ካርታ 6 እና 7)፡፡ በሌላ በኩል በመካከለኛው፣ በደቡብ ምዕራብ፣ ምዕራብ እና ሰሜን ምስራቅ የሀገራችን አከባቢዎች ላይ አልፎ አልፎ ከሚጠናከሩት የአየር ሁኔታ ክስተቶች ላይ በመነሳት ቅፅበታዊ ጎርፍ ሊያስከትል የሚችል ከባድ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚኖር የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡




ካርታ 6 እ.ኤ.አ. ከኦገስት 21-31, 2025 የሚኖረዉ የዝናብ መጠን በሚ.ሜ

በመሆኑም ከባለፉት የክረምት ወራት ጀምሮ ከመደበኛና ከመደበኛ በላይ ዝናብ አግኝተዋል፡፡ በሚቀጥሉት ቀናትም ከመደበኛ በላይ የዝናብ መጠንና ስርጭት የሚኖር ሲሆንና ይህም ሁኔታ የጎርፍ ተጋላጭ በሆኑት አከባቢዎች ላይ ተጽዕኖ እንዳይደርስ አስፈላጊዉን ቅድመ ጥንቃቄና ዝግጅት ማድረግ እንደሚያስፈልግ የኢትዮጵያ ሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት ይጠቁማል (ካርታ 6 እና 7) ፡፡

በሚቀጥሉት አስራ አንድ ቀናቶች ከሚጠናከሩት የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ላይ በመነሳት የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ በሆኑ የሀገሪቱ አከባቢዎች ብዙ ቦታዎቻቸውን የሚሸፍን ከመካከለኛ እስከ ከባድ (ከ11-30 ሚ.ሜ) መጠን ያለው ዝናብ ያገኛሉ፡፡ በተጨማሪም በውሃ አካላትና በከባቢ አየር ውስጥ ከሚጠናከሩት የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ላይ በመነሳት በምስራቅ፣ ሰሜን ምስራቅ፣ መካከለኛው፣ ምዕራብ፣ ሰሜን ምዕራብ፣ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ በ24 ሠዓት ውስጥ ከ30 ሚ.ሜ በላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚያገኙ አሃዛዊ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ (ካርታ 7)፡፡



ካርታ 7 እ.ኤ.አ. ከኦገስት 21-31, 2025 የሚኖረዉ ከፍተኛ የዝናብ መጠን


ሠንጠረዥ 1፡ በሚቀጥሉት አስራ አንድ ቀናት ዝናብ የሚያገኙ አከባቢዎችና በ24 ሰዓት ዉስጥ የሚኖረዉ የዝናቡ መጠን

| ክልል | ዞን | በ 24 ሰዓት ዉስጥ የሚኖረዉ የዝናቡ መጠን |
|---|---|---|
| አሮሚያ | የቄለም ወለጋ፣ ምዕራብ ወለጋ፣ ምስራቅ ወለጋ፣ ሆሮ ጉድሩ ወለጋ፣ ኢሉባቦር፣ ቡኖ በደሌ፣ ጅማ፣ የሰሜን፣ ምዕራብ፣ ምስራቅ፣ ደቡብ ምዕራብ ሸዋ ዞኖች፣ ምዕራብ አርሲ እና አርሲ፣ | ከባድ መጠን (ከ30 ሚ.ሜ በላይ) |
| | ምዕራብ ሐረርጌ፣ ምስራቅ ሐረርጌ፣ ባሌ፣ ምስራቅ ባሌ፣ ምዕራብ ጉጂ፣ ጉጂ እና ቦረና ዞኖች | ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን (ከ1-29 ሚ.ሜ) |
| አማራ | የሰሜን፣ ምዕራብ፣ መካከለኛዉ እና ደቡብ ጎንደር፣ የባህርዳር ዙሪያ፣ የአዊ፣ የሰሜን፣ ምዕራብ እና ምስራቅ ጎጃም፣ የዋግ ህምራ፣ የሰሜን ሸዋ ዞኖች፣ የሰሜን እና ደቡብ ወሎ ዞኖች | ከባድ መጠን (ከ30 ሚ.ሜ በላይ) |
| ትግራይ | የምዕራብ፣ የሰሜን ምዕራብ፣ የመካከለኛዉ፣ የደቡብ ምስራቅ እና የደቡብ ትግራይ ዞኖች | ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን (ከ11 እስከ 30 ሚ.ሜ) |

| | | |
|---|---|---|
| አፋር | የማሂ፣ ሀሪ፣ ቅልበቲ፣ ፊንቲ፣ ሀውሲ እና ጋቢ ዞኖች | ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን (ከ11 እስከ 30 ሚ.ሜ) |
| ቤንሻንጉል ጉምዝ | የካማሺ፣ መተከል፣ አሶሳ፣ ማኦ ኮሞ ዞኖች | ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን (ከ11 እስከ 30 ሚ.ሜ) |
| ጋምቤላ | የአኝዋክ፣ መዠንግ፣ የኑዌር እና የኢታንግ ልዩ ወረዳ | ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን (ከ11 እስከ 30 ሚ.ሜ በላይ) |
| ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ | የከፋ፣ ኮንታ፣ ዳውሮ፣ ቤንች ሸኮ፣ ሸካ እና ምዕራብ ኦሞ | ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን (ከ11 እስከ 30 ሚ.ሜ) |
| ማዕከላዊ ኢትዮጵያ | ጉራጌ፣ ምስራቅ ጉራጌ፣ ስልጤ፣ ሀዲያ፣ ከምባታ፣ ሀላባ፣ የም፣ ጠምባሮ ልዩ ወረዳ፣ ቀቤና ልዩ ወረዳ፣ ማረቆ ልዩ ወረዳ | ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን (ከ11 እስከ 30 ሚ.ሜ) |
| ሲዳማ ክልል | ሁሉም የክልሉ ዞኖች | ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን (ከ11 እስከ 30 ሚ.ሜ) |
| አዲስ አበባ፤ ድሬዳዋ እና ሐረሪ | | ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን (ከ11 እስከ 30 ሚ.ሜ) |
| ደቡብ ኢትዮጵያ | የወላይታ፣ ጎፋ፣ ጋሞ፣ እና ባስኬቶ | ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን (ከ11 እስከ 30 ሚ.ሜ) |
| | ጌድዮ፣ አሪ፣ ኮንሶ፣ ቡርጂ፣ አሌ፣ ጋርዱላ፣ ኮሬ እና ደቡብ ኦሞ ዞኖች | ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን (ከ1 እስከ 29 ሚ.ሜ) |
| ሶማሌ | ሲቲ እና ፋፈን ዞኖች | ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን (ከ11 እስከ 30 ሚ.ሜ) |
| | የኤረር፣ ጃረር፣ ነጎብ፣ ቆራሂ እና ዳዋ፣ ዞኖች | ቀላል መጠን (ከ1-10 ሚ.ሜ) |

## 2.3 የሚኖረው የቀኑ ከፍተኛ የሙቀት ሁኔታ

በኦገስት ሶስተኛዉ አስራ አንድ ቀናት ከሚኖረው የፀሐይ ሀይል ጋር በተያያዘ የቀኑ ከፍተኛ ሙቀት በኤሊዳር፣ ዱብቲ፣ ሰመራ፣ ቡሬ፣ አሳይታ፣ ሁንዱፎ፣ ገዋኔ፣ ሚሌ፣ ዳሊፋጊ፣ አይሻ፣ ጉሊና፣ አዋሽ አርባ፣ ባቲ፣ ዶሎ ኦዶ፣ ዳዋ፣ ጎዴ፣ አቦቦ፣ ቋራ፣ አዋሽ ፈንታሌ፣ ጭፍራ፣ ላሬ፣ መተሃራ እና ፉኙዶ አከባበዎች ላይ ከ30 እስከ 38 ዲግሪ ሴልሺየስ እንደሚሆን አሃዛዊ ትንበያዎች ያመላክታሉ (ካርታ 8)፡፡




ካርታ 8 እ.ኤ.አ. ከኦገስት 21-31, 2025 የሚኖረዉ ከፍተኛ የሙቀት መጠን በዲ.ሴ

## 2.4 እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 1 እስከ 10/2025 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ

በመጪዎቹ የሴፕቴምበር የመጀመሪያዎቹ አሥር ቀናት ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ አካባቢዎች በተለይም በምዕራብ አጋማሽ እንዲሁም በመካከለኛው የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ ተጠናክሮ ይቀጥላል፡፡ በተጨማሪም በመካካለኛው፣ ምዕራብ፣ ደቡብ ምዕራብ እንዲሁም ሰሜን ምዕራብ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ጠንካራ እና የተስፋፋ የዝናብ መጠንና ስርጭት እንደሚኖራቸው አሀዛዊ የትንበያ መረጃዎች ያመላክታሉ፡፡ በሌላ በኩል ከሚጠናከሩ የደመና ክምችቶች ላይ በመነሳት በመካከለኛው፣ ሰሜን ምዕራብ፣ ምዕራብ እና ደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ በ24 ሰዓት ውስጥ ከ30 ሚ.ሜ በላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ይኖረቸዋል ፡፡

## 2.5 እ.አ.አ ከኦገስት 21 እስከ 31/2025 የሚኖረው የአየር ሁኔታ በግብርናው ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥሉት አሥራ አንድ ቀናት የምዕራብ፣ የሰሜን ምዕራብ፣ የሰሜን ምስራቅ፣ የምስራቅ እና የመካከለኛዉ የሀገሪቱ ቦታዎች ላይ ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን ያለዉ እርጥበት ይኖራቸዋል፡፡ እንዲሁም ደቡብ ምዕራብ እና ደቡብ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው እርጥበት ይጠበቃል፡፡ ይህም የሚጠበቀው እርጥበት ለወቅቱ የግብርና ስራ እንቅሥቃሴ በአመዛኙ አዎንታዊ ሚና የሚኖረው ቢሆንም፣ ተያያዥ ስጋቶችን ለመቀነስና የሚኖሩትን መልካም አጋጣሚዎች

# በኢትዮጵያ የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ፣

## ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ እና ምክር አገልግሎት ምርምር ዘርፍ

በላቀ ሁኔታ ለመጠቀም የቀረቡትን ቦታ ተኮር የግብርና ሚቲዎሮሎጂ ምክረ ሀሳቦች በሁሉም ደረጃ በተገቢው ሁኔታ መተግበር ያስፈልጋል።

ሠንጠረዥ 2፡ በሚቀጥሉት አስራ አንድ ቀናት የሚኖረዉ የእርጥበት ሁኔታ በግብርናው እንቅስቃሴ ላይ

| ዞኖች | የእርጥበት ሁኔታ | አዎንታዊ ተጽዕኖ | አሉታዊ ተጽዕኖ | የተሰጠ ምክረ ሃሳብ |
|---|---|---|---|---|
| **የክረምት እርጥበት ተጠቃሚ የመኸር አምራች ዞኖች** | | | | |
| የቄለም ወለጋ፣ ምዕራብ ወለጋ፣ ምስራቅ ወለጋ፣ ሆሮ ጉድሩ ወለጋ፣ ኢሉባቦር፣ ቡኖ በደሌ፣ ጅማ፣ የሰሜን፣ ምዕራብ፣ ምስራቅ እና ደቡብ ምዕራብ ሸዋ ዞኖች፣ የሰሜን፣ ምዕራብ፣ መካከለኛዉ እና ደቡብ ጎንደር፣ የባህርዳር ዙሪያ፣ የአዊ፣ የሰሜን፣ ምዕራብ እና ምስራቅ ጎጃም ዞኖች የዋግ ህምራ፣ የምዕራብ፣ የሰሜን ምዕራብ፣ የመካከለኛዉ ትግራይ፣ የካማሺ፣ መተከል፣ አሶሳ፣ ማኦ ኮሞ ዞኖች፣ የአኝዋክ፣ መዥንግ፣ የኑዌር እና የኢታንግ ልዩ ወረዳ፣ የከፋ፣ ኮንታ፣ ዳውሮ፣ ቤንች ሸኮ፣ ሸካ እና ምዕራብ ኦሞ ዞኖች | ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን ያለዉ እርጥበት | • የአፈር ውስጥ እርጥበት መሻሻል<br>• ለረጅምና መካከለኛ ጊዜ ሰብሎች እድገት<br>• ለቋሚ ተክሎችና ለግጦሽ ሳር ዕድገት<br>• የመጠጥ ውሃ አቅርቦት መሻሻል | • በሰብሎች ላይ የውሃ መተኛት<br>• ተዳፋታማ በሆኑ አካባቢዎች የአፈር መሸርሸር እና የመሬት መንሸራተት<br>• የአረም መስፋፋት<br>• የአፈር ማዳበሪያ መታጠብ<br>• የበረዶ ክስተት | • የውሃ ማንጣፈፍያ እና የጎርፍ መቀልበሻ ቦዮችን ማዘጋጀት<br>• የማዳበሪያም ሆነ የጸረ ተባይ እና አረም እርጭትን በትክክለኛው ሰዓት መተግበር |
| **በልግ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸውና የመኸር አብቃይ የሆኑ ዞኖች** | | | | |
| ምዕራብ አርሲ እና አርሲ፣ ሰሜን እና ደቡብ ወሎ እና የሰሜን ሸዋ ዞኖች፣ የደቡብ ምስራቅ እና የደቡብ ትግራይ ዞኖች፣ ጉራጌ፣ ምስራቅ ጉራጌ፣ ስልጤ፣ ሀዲያ፣ ከምባታ፣ ሀላባ፣ የም፣ ጠምባሮ ልዩ ወረዳ፣ ቀቤና ልዩ ወረዳ፣ ማረቆ ልዩ ወረዳ፣ ሁሉም ሲዳማ የክልሉ ዞኖች፣ አዲስ አበባ፣ ድሬዳዋ እና ሐረሪ የወላይታ፣ ጎፋ እና ባስኬቶ፣ የማሂ፣ ሀሪ፣ ቀልበቲ፣ ፈንቲ፣ አውሲ እና ጋቢ ዞኖች ፣ሲቲ እና ፋፈን ዞኖች | ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን ያለዉ እርጥበት | • ለረጅምና መካከለኛ ጊዜ ሰብሎች እድገት<br>• ለቋሚ ተክሎችና ለግጦሽ ሳር ዕድገት በቂ እርጥበት መኖር<br>• ለእንስሳት መኖና የመጠጥ ውሃ አቅርቦት መሻሻል | • በሰብሎች ላይ የውሃ መተኛት<br>• የአፈር መሸርሸር<br>• የአረም መስፋፋት<br>• የበረዶ ክስተት | • የውሃ ማንጣፈፍ ስራዎችን መስራት<br>• የጎርፍ መቀልበሻ ቦዮችን ማዘጋጀት<br>• የማዳበሪያ አጠቃቀምን በትክክለኛው ሰዓት መተግበር<br>• አረምን በወቅቱ ማረም፣ ፀረ-አረምና ፀረ-ተባይ ኬሚካሎችን ከግብርና ባለሙያ ጋር በመመካከር መተግበር |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ምዕራብ ሐረርጌ፣ ምስራቅ ሐረርጌ እና ባሌ | ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለዉ እርጥበት | • ለረጅምና መካከለኛ ጊዜ ሰብሎች እድገት ለእንስሳት መኖና የመጠጥ ውሃ አቅርቦት መሻሻል | | • የሚገኘውን እርጥበት በአግባቡ መጠቀም<br>• በቆላማ አካባቢዎች የሚገኘውን የዝናብ ውሀ ማሰባሰብ |
| በልግ ዋነኛ የዝናብ ወቅታቸዉ የሆኑ ዞኖች | | | | |
| ምስራቅ ባሌ፣ ምዕራብ ጉጂ፣ ጉጂ እና ቦረና ዞኖች፣ ጋሞ፣ ጌድዮ፣ አሪ፣ ኮንሶ፣ ቡርጂ፣ አሌ፣ ጋርዱላ፣ ኮሬ እና ደቡብ ኦሞ ዞኖች፣ የኤረር፣ ጃረር፣ ነጎብ፣ ቆራሂ እና ዳዋ ዞኖችች | ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለዉ እርጥበት | • የዝናብ ውሃ ለማሰባሰብና ለማጠራቀም<br>• ለእንስሳት መኖና የመጠጥ ውሃ አቅርቦት | • ከፍተኛ ትነት መኖር | የዝናብ ውሃን በማሰባሰብ በደረቅ ሰሞናት ተግባር ላይ ማዋል |

## 2.6 እ.ኤ.አ ከኦገስት 21 እስከ 31/2025 የሚኖረው የአየር ሁኔታ በውሃ ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በቀጣይ የኦገስት ሶስተኛ አስር ቀናት በአብዛኛው የክረምት ተጠቃሚ በሆኑ ተፋሰሶች ላይ ከመጠነኛ እስከ ከፍተኛ መጠን ያለው የገፀ ምድር የውሃ ፍሰት ያገኛሉ፡፡ ይህም ሁኔታ የገጸ ምድር እና የከርሰ ምድር የውሀ ሀብታችንን ከማበልጸግ አንጻር አዎንታዊ ጎን ቢኖረውም  በአንጻሩ ግን ከሚኖረው ተደጋጋሚ የሆነ ከባድ ዝናብ ጋር ተያይዞ በተለይም ለጎርፍ ተጋላጭ በሆኑ ተፋሰሶች ላይ  ቅፅበታዊ ጎርፍም ሆነ የወንዞች መጥለቅለቅ በተለይም በአዋሽ ተፋሰስ አዋሽ ወንዝ ዳርቻ፣ በኦሞ ጊቤ ተፋሰስ ኦሞ ወንዝ ዳርቻ እንዲሁም በተፋሰሶች ረባዳማ አካባቢዎች በሚኖሩ የሕብረተሰብ ክፍሎች ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ሊያስከትል ይችላል፡፡ በሌላ በኩል ባለፉት ቀናት ወደ ግድቦች የሚገባው የገጸ ምድር የውሃ ፍሰት ከፍተኛ ከመሆኑ ጋር ተዳምሮ በቀጠይ አስር ቀናትም የሚጠበቀው ከፍተኛ የውሀ ፍሰት በተከዜ፣ በፊንጫ፣ በጣና በለሥ እና በቆቃ የታችኛው ተፋሰሶች ላይ ስጋት ሊፈጥር ይችላል፡፡ በመሆኑም የሚመለከታቸው የዘርፉ አካላት ሊኖር የሚችለው  አደጋ ለመቀነስም ሆነ መልካም ዕድሎችን በላቀ ሁኔታ ለመጠቀም የቀረቡትን ተፋሰስ ተኮር የውሃ ሚቲዎሮሎጂ ምክረ ሀሳቦች ተግባራዊ ያድርጉ፡፡

ሠንጠረዥ 3፡ በሚቀጥሉት አስራ አንድ ቀናት የሚኖረዉ የእርጥበት ሁኔታ በዉሃዉ ዘር ላይ ሊኖር የሚችለው ተጽዕኖ

| የውኃ ተፋሰሶች | የእርጥበት ሁኔታ | አዎንታዊ ተጽዕኖ | አሉታዊ ተጽዕኖ | የውኃ ሚቲዎሮሎጂ ምክረ ሃሳብ |
|---|---|---|---|---|
| በአብዛኛው ተከዜ፣አባይ፣ባሮ አኮቦ፣አዋሽ፣ኦሞ ጊቤ፣መረብ ጋሽ፣ አፋር ደናክል፣ አይሻ፣ላይኛው እና መካከለኛ ስምጥ ሸለቆ፣ በላይኛው ዋቢ ሸበሌ እና ገናሌ ዳዋ | ከመካከለኛ እስከ ከፍተኛ እርጥበት | የመስኖም ሆነ የሃይል ማመንጫ ግድቦች ውሀ መጠን መጨመር<br>የገፀ ምድር የውሃ ፍሰት መጨመር<br>የከርሰ ምድር የውኃ መጠን መሻሻል<br>የመጠጥ ውኃ አቅርቦት ሽፋን መጨመር | የወንዞች መሙላት<br>የቅፅበታዊ ጎርፍ ስጋት መጨመር<br>በውሃ መያዣዎች ላይ የደለል ስጋት መጨመር<br>• የፍሳሽ መውረጃዎች በደለል እንዲሁም በጠጣር ቆሻሻ መዘጋት | • የጎርፍ መቀለበሻ ቦዮችን ማዘጋጀት<br>• ፍሳሽ ሊዘጉ የሚችሉ ቆሻሻዎች በተገቢ ሁኔታ ማስወገድ<br>• የጎርፍ መውረጃዎች ቦዮችን ማፅዳት<br>• ወራጅ ውሀን በእግርም ሆነ በቀላል ተሽከርካሪ ለማቋረጥ አለመሞከር<br>• የዝናብ ውሀ ማሰባሰብና ማጠራቀም<br>• የጎርፍ ተጽዕኖ ትንበያዎችንና ምክረ ሀሳቦችን በየጊዜው መከታተል |
| • በአብዛኛው መካከለኛው እና የታችኛው ገናሌ ዳዋ፣ ዋቤ ሸበሌ እና ኦጋዴን | ከመጠነኛ እስከ ደረቅ ሁኔታ | • በጎርፍ ሆነ በደለል ስጋት አለ መኖር | • ዝቅተኛ የውሀ ፍሰት<br>• እርጥበት አጠር በሆኑ አካባቢዎች የውሃ እጥረት<br>• ከፍተኛ ትነት | • የሚገኘው መጠነኛ የዝናብ ውሃ ከጣራ እና ከመሬት ወለል በተግቢ ሁኔታ ማሰባሰብ<br>• የውሀ ሀብትን በአግባቡ መጠቀም<br>የሚገኘውን መጠነኛ የዝናብ ውሀ ከብክነት እና ከብክለት በመከላከል |

Ethiopian Meteorology Institute